# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1028/2017 ዓ.ም

**የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1028/2017 ዓ.ም**

የግብርና ሚኒስቴር በንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 660/2008 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1028/2017 ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሃረጉ አግባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 660/2002 ነው፡፡
2) **"ደንብ"** ማለት የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ የሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 372/2008 ነው፡፡
3) **"አግባብ ያለው አካል"** ማለት የግብርና ሚኒስቴር ወይም በክልል ግብርና የሚመለከተው የመንግስት ተቋም ነው፡፡
4) **"ተቆጣጣሪው አካል"** ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ወይም የክልል ተቆጣጣሪ አካል ነው፡፡
5) **"አፅቂ ነፍሳት"** ማለት የጀርባ አጥንት የሌላቸው ነፍሳት ማለት ነው፡፡
6) **"በዘመናዊ መንገድ ማነብ"** ማለት ባለፍሬም ወይም የሽግግር ወይም ባህላዊ ቀፎዎችን እና ዘመናዊ ወይም የተሻሻሉ የማናቢያ ቁሳቁሶችንና ግብዓቶችን በመጠቀም ለንቦች የሚያስፈልጉ መጠለያ በማዘጋጀት፣ የንብ ቀሰም ዕፅዋቶችን በማልማት ወይም በመንከባከብ ወይም እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ መኖን በመመገብ የሚከናወን የንብ ዕርባታ ስራ ነው፡፡

7) **"ዘረ-መል"** ማለት ተወራራሽ ባህሪያትን የሚያስተላልፍ በማንኛውም ሕይወት ያለው ነገር ውስጥ የሚገኝ የዘር ውርስ ክፍል ነው፡፡

8) **"ንፅህና"** ማለት የንብ እርባታ ቦታን፣ የማነቢያ ቁሳቁስን፣ የንብና የንብ ዉጤቶች ማቀነባበሪያ፣ማከማቻና ማጓጓዣን ከኬሚካል፣ ከባዕድ ሽታ እና ከንብ ጠላት ነፃ ማድረግ ነው፡፡

9) **"ባዕድ ነገር"** ማለት የንብ ውጤቶችን ተፈጥሮአዊ ባህሪይና ይዘት የሚለውጥ ማንኛውም ነገር ነው፡፡

10) **"የንግድ አዋጭነት ዕቅድ"** ማለት በንብ ሀብት ልማት ወይም የንብ ውጤቶች ንግድ ወይም የቅድመና የድህረ ምርት ንብ ማነቢያ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች ማምረትና ንግድ ስራ ላይ የሚሰማራ ሰው የሚያቀርበው ዝርዝር የስራ እቅድ ነው፡፡

11) በአዋጅ እና በደንብ የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት አላቸው፡-

# ክፍል ሁለት

# የአናቢዎች ምዝገባ እና የማነቢያ ሥፍራ አወሳሰን

## 3. የአናቢዎች ምዝገባ

1) ማንኛውም በከተማም ሆነ በገጠር የሚኖር አናቢ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሀብረ-ንቦችን በግዢ፣በዑደት፣በስጦታም ሆነ በማራባት ያገኘውን ሀብረ-ንብ በዘመናዊ መንገድ የሚያነባ ከሆነ በቀፎው ውስጥ ሀብረ-ንብ ካስገባበት ቀን ጀምሮ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ አግባብ ያለው አካል በሚገኝበት ወረዳ ወይም ቀበሌ ጽ/ቤት ማስመዝገብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ሀብረ-ንቡን ያስመዘገበ አናቢ አዲስ ሀብረ-ንብ በግዢ ወይም በስጦታ ወይም አባዝቶ ወይም በዑደት ምክንያት የተገኘውን ሀብረ-ንብ ወደ ቀፎ ሲያስገባ የተገኘውን አዲስ ሀብረ-ንብ ካስገባበት ቀን ጀምሮ በ 15 ቀናት ጊዜ ውስጥ አግባብ ያለው አካል ማስመዝገብ አለበት፡፡

3) አግባብ ያለው አካል አገራዊ መረጃ ለመያዝ ያስችለው ዘንድ ለሀብረ-ንቦች መለያ ይሰጣል፡፡

4) አግባብ ያለው አካል አናቢው ሀብረ-ንቡን እንዳስመዘገበ መለያ መስጠት አለበት፡፡

5) ማንኛውም አናቢ አግባብ ካለው አካል መለያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ ቀፎው ላይ ማድረግ አለበት፡፡

6) አናቢው አስመዝግቦት የነበረ ህብረ-ንብ በተለያዩ ምክንያቶች ቀፎውን ለቆ የሄደ ከሆነ ከለቀቀበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው አካል ማሳወቅ ያለበት ሲሆን አግባብ ያለው አካልም መለያውን ይሰርዛል፡፡

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ህብረ-ንብ ቀፎው ውስጥ የገባበት ወይም ያስገባ አናቢ የህብረ-ንቡ ባለቤት ስለሚሆን በእጁ በገባ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው አካል ማስመዝገብ አለበት፡፡

## 4. የማነቢያ ስፍራ አወሳሰን

1) በከተማ ንብ የማነብ ስፍራ ሲወሰን አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ. ለንብ ቀሰምነት ጠቃሚ የሆኑና በተለያዩ ወቅቶች የሚያብቡ ዕፅዋቶች በአካባቢው መኖር ወይም ማልማት፤

ለ. ንፁህ ውሃ በማነቢያ ስፍራ ውስጥ ማቅረብ መቻሉን ማረጋገጥ፤

ሐ. መሬቱ ረግረጋማ ያልሆነና በጎርፍ የማይጠቃ መሆኑን፤

መ. ለትራንስፖርት አመቺ መሆኑን፤

ሠ. ከማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ መስመር ከሚያልፍበት፣ ቆሻሻ ከሚጠራቀምበት ቦታ እና ከመኖሪያ አካባቢ ቢያንስ 50 ሜትር የራቀ መሆን አለበት፤

ረ. የማናቢያ ስፍራው የመብረሪያ አቅጣጫ ከ3 ሜትር ያላነሰ ከፍታ ባለው የግንብ፣ የንብ ቀሰም እፅዋት ወይም የጠቅጣቃ ሽቦ አጥር በማጠር ህብረ-ንብ ያለበትን ቀፎ መቀመጡን፤

ሰ. ኬሚካል ከሚያቦኑ ወይም ከሚያተኑ ፋብሪካዎች ቢያንስ 2 ኪ.ሜ የራቀ መሆኑን፤

ሸ. ተደጋጋሚ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በብዛት የማይካሄድበት አካባቢ መሆን አለበት

2) በገጠር ንብ የማነብ ስፍራ ሲወሰን አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡

ሀ. ለንብ ቀሰምነት ጠቃሚ የሆኑና በተለያዩ ወቅቶች የሚያብቡ ዕፅዋቶች በአካባቢው መኖር ወይም ማልማት፤

ለ. ንፁህ ውሃ ከ0.5 እስከ 1 ኪ.ሜ መኖሩን ወይም በማነቢያ ስፍራ ውስጥ ዉሃ ማቅረብ መቻሉን ማረጋገጥ፤

ሐ. መሬቱ ረግረጋማ ያልሆነና በጎርፍ የማይጠቃ መሆኑን፤

መ. ለትራንስፖርት አመቺ መሆኑን፤

ሠ. ከማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ መስመር ከሚያልፍበት፣ቆሻሻ ከሚጠራቀምበት ቦታ 100 ሜትር የራቀ መሆኑን፤

ረ. የማነቢያ ስፍራው ከመኖሪያ ቤት 50 ሜትር መሆኑን፤

ሰ. ኬሚካል ከሚያቦኑ ወይም ከሚያተኑ ፋብሪካዎች ቢያንስ 2 ኪ.ሜ የራቀ መሆኑን፤

ሸ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በብዛት የማይካሄድበት አካባቢ መሆኑን፤

3) የንግድ ንብ ልማት የማነብ ስፍራ ሲወሰን አግባብ ያለው አካል የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ. ከማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ መስመር ከሚያልፍበት፣ ቆሻሻ ከሚጠራቀምበት እና ከመኖሪያ ቤት 100 ሜትር የራቀ መሆኑን፤

ለ. ኬሚካል ከሚያቦኑ ወይም ከሚያተኑ ፋብሪካዎች ቢያንስ 2 ኪ.ሜ የራቀ መሆኑን፤

ሐ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በብዛት የማይካሄድበት አካባቢ መሆኑን፤

መ. ከሌላ የንግድ ንብ ልማት ጣቢያ ቢያንስ ከ 3 ኪ.ሜ ርቀት ያለው መሆኑን፤

ሠ. ለማናቢያ የሚገለግሉ የተሟሉ ቁሳቁሶች መኖራቸውን፤

ረ. እራሱ የሰለጠነ እና የምስክር ወረቀት ያለው ወይም የሰለጠነና የምስክር ወረቀት ያለው ሰው ቀጥሮ ማሰራት አለበት፤

ሰ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከ ሀ እስከ መ የተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟላት፡፡

## 5.የህብረ-ንቦች ውደት

1) ማንኛውም በውደት ላይ የተገኘ ህብረ-ንብ ከአረፈበት ቦታ በሚያዝበት እና ወደ ተዘጋጀለት ቀፎ ለማስገባት ሲጓጓዝ አስፈላጊውን ሙሉ የንብ መከላከያ አልባሳትና የውሃ ርጭት በመጠቀም በጠቅጣቃ ሽቦ ወይም አየር ሊያስገባ በሚችል ጨርቅ በመሸፈን ንቦችን በማይጎዳ መልኩ መሆን አለበት፤

2) ወደ ቀፎ ማስገባት ካልተቻለ ንቦቹን በማያስወጣና አየር ሊያስገባ በሚችል ጠቅጣቃ ሽቦ፣ ጨርቅ፣ ሰሌን፣ ካርቶን መጓጓዝ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## የንግስት ንብ ርቢ፣ የማነቢያ መሣሪያዎች ማምረትና ምርምር

### 6. የንግድ ንግስት ንብ ርቢ

1) ማንኛውም የንግድ ንግስት ንብ ርቢ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡
2) ማንኛውም በንግስት ንብ ርቢ ንግድ ስራ የተሰማራ ሰው ከተቆጣጣሪ አካል ንግስት ንብ የማባዛትና የማሰራጨት ወይም የማባዛትና የመሸጥ ፍቃድ ተሰጥቶአቸው ከሚሰሩ ማዕከላት ለመነሻ እናት ንብ መጠቀም አለበት፡፡
3) ለንግድ ለንግስት ንብ ርቢ የሚውል ጣቢያ ወይም ማዕከል ለማቋቋም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን የመምረጫ መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-
   ሀ. በመካከላቸው ቢያንስ 300 ሜትር ርቀት ያላቸው ሁለት የቀፎ ማስቀመጫ ጥላ/ጋጣ/ ማዘጋጀት፤
   ለ. ለንግሥት ንብ ማራቢያ የሚያገለግሉ የተሟሉ ቁሳቁሶች መኖር፤ እና
   ሐ. በንግስት ንብ ርቢ እራሱ የሰለጠነ እና የምስክር ወረቀት ያለው ወይም የሰለጠነና የምስክር ወረቀት ያለው ሰው ቀጥሮ ማሰራት አለበት፡፡

### 7. የማነቢያ መሳሪያዎች ማምረት

1) ለቅድመ-ምርት አገልግሎት የሚውሉ ማናቸውም የንብ ማነቢያ መሳሪያዎች ማምረት ላይ የተሰማራ ሰው ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ማምረት አለበት፡፡
2) ለድህረ-ምርት አገልግሎት የሚውሉ ማናቸውም የማቀነባበሪያና ማከማቻ መሳሪያዎች ማምረት ላይ የተሰማራ ሰው ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ማምረት አለበት፡፡
3) በአገር ውስጥ የሚመረቱትና ከውጪ የሚገቡ የንብ ማነቢያ፣ የማቀነባበሪያና ማከማቻ መሳሪያዎች ጥራትና ደረጃቸውን ጠብቀው ለገበያ መቅረባቸውን በተቆጣጣሪው አካል ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡

## 8.የአድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

ማንኛውም ሰው በንግድ ንብ ልማት፣ ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረት፣የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ተቆጣጣሪውን አካል ሳያስፈቅድ የድርጅቱን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዛወር ወይም የባለቤትነት ለውጥ ማድረግ አይችልም።

## 9.በንብ ዝርያ ማሻሻል፣ የማናቢያ መሳሪያዎች እና በንብ ውጤቶች ላይ ምርምር ስለማካሄድ

1) ማንኛውም የውጪ አገር ዜጋ በንብ ዘር ማሻሻል፣ በንብ ውጤቶች፣ በማር ዕፅዋትና በንቦች አጠቃላይ እንክብካቤ ላይ ምርምር ለማካሄድ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

ሀ. ማንነቱን የሚገልፅ መረጃ፣ የመጣበትን ዓላማ እና የቆይታ ጊዜውን ለሚመለከተው አካል ማቅረብ አለበት፤

ለ. በንብ ሀብት ልማት ስፔሻላይዝድ ያደረገበት ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፤

ሐ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1(ለ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተመራማሪው በትምህርት ሂደት ላይ እያለ ከሆነ የተማሪነት ማስረጃ ማምጣት አለበት፤

መ. ምርምር ለማካሄድ በሚመጣበት ወቅት ከሀገር ውጪ ያሉ የንብ ዝርያዎችን ይዞ አለመምጣቱን ስልጣን በተሰጠው አካል መረጋገጥ አለበት፤

ሠ. ለምርምሩ የሚረዱ የምርምር ቁሳቁሶች ካሉት ስለትክክለኛነታቸው ስልጣን በተሰጠው አካል ማስፈተሸና ማስመዝገብ እንዲሁም እቃውን ለማስገባት የተሰጠውን ፍቃድ ማያያዝና ማቅረብ አለበት፤

ረ. በንብ ዘር ማሻሻል የምርምር ስራ ሊያካሂድ የሚችለው የንብ ንዑስ ዝርያዎች በሚገኙበት ስነ-ምህዳር ክልል ውስጥ ብቻ መሆን አለበት፤

ሰ. ስለሚመራመረው ነገር ዝርዝር ሁኔታ የሚገልፅ ዝርዝር የስራ ዕቅድ ማቅረብ አለበት፤

ሸ. በቆይታ ጊዜ ውስጥ የሀገሪቱን የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ ህጎችና ሌሎች ህጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፤

ቀ. ምርምር ለማድረግ በሚሄድባቸው ቦታዎች በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ማንነቱን የሚገልፅ መረጃ መያዝና በሚሄድበት ወቅት ለሚመለከተው አካል የሚዘዋወርባቸውን አካባቢዎች የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤

በ. የምርምር ስራውን እንዳጠናቀቀ ውጤቱን ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

2) ከምርምር ውጤት በኋላ የሀገሪቱን የንብ ዝርያዎች ይዞ መውጣት የተከለከለ ነው፡፡

## 10. የንብ ዘርን በማዳቀል ስለማሻሻል

1) ማንኛውም የንብ ዘር በማዳቀል የዝርያ ማሻሻል ስራ ሊከናወን የሚችለው በመንግስት ስልጣን በተሰጠው ተቋም ወይም በተቆጣጣሪው አካል ፍቃድ በተሰጣቸው የግልና የማህበር ተቋም ብቻ ይሆናል፡፡

2) ማንኛውም የንብ ዘር በማዳቀል የዝርያ ማሻሻል ስራ የሚሰራ ሰው የሀገሪቱን የንብ ሀብት ልማትና ጥበቃ እና ሌሎች ህጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

3) በማዳቀል የሚገኝ የተሻሻለ አዲስ የንብ ዘር የሚመዘገበው በብሔራዊ ደረጃ በሚቋቋመው በዝርያ ወይም ዘር አጽዳቂ ኮሚቴ ግምገማ ውጤት መሠረት በተቆጣጣሪ አካል ሲፀድቅ ነው፡፡

4) በማዳቀል የሚገኝ የተሻሻለ አዲስ የንብ ዘርን ያገኘ ማንኛውም ሰው የተሟላ የርቢ መረጃን ለዝርያ ወይም ለዘር አጽዳቂ ኮሚቴ በመስጠት የማጸደቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 11. በማዳቀል የተገኘ የንብ ዘር ስለመመዝገብ

1) ማንኛውም በማዳቀል የተገኘ የንብ ዘር መመዝገብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 መሰረት በማዳቀል የተገኘ የንብ ዘር መመዝገብ የሚችለው፡-

ሀ) በዋነኛነት ምርታማነታቸው፣ አነስተኛ የመናደፍ ባህሪያቸው፣ የቀፎ ውስጥ ፅዳት ችሎታቸው፣ አነስተኛ ዑደትና ኩብለላ፣ በሽታንና ድርቅን የመቋቋም አቅማቸው እና አካባቢውን የመላመድ ብቃታቸው በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

3) ለ) አዳቃዩ ይመዝገብልኝ ብሎ ከጠየቀበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያላቸው የምርታማነትና ሌሎች ባህሪያቶች ታይተው ለንብ ሀብት ልማት ይውላሉ ተብሎ ከታመነባቸው ብቻ ነው፡፡ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) የተጠቀሰው

እንደተጠበቀ ሆኖ የተዳቀሉ ኅብረ-ንቦችን በተመረጡ አናቢዎችና በማሰልጠኛ ተቋማት ላይ ሙከራ በማድረግ ውጤታማነታቸው በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ከተረጋገጠ በኋላ ማሰራጨት ይቻላል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በማዳቀል የተገኙት ንቦች ውጤታማ ካልሆኑ ምዝገባው አይካሄድም፡፡

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የተዳቀሉት ንቦች ሌላ ጉዳት እንደሚያደርሱ በተቆጣጣሪው አካል ከተረጋገጠ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## የንብ ውጤቶች አቀነባበር፣ አስተሻሸግ፣ አያያዝ፣ ምልክት አደራረግና አጓጓዝ

### 12. ስለንብ ውጤቶች ማቀነባበርያና ማሸጊያ የህንፃ ግንባታ

ለንብ ውጤቶች ማቀነባበርና ማሸግ አገልግሎት የሚውል ህንፃ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

1) የሚገነባው ህንፃ ቢያንስ የሰራተኞች ንፅህና መጠበቂያና ልብስ መቀየሪያ ክፍል፣ ያልተጣራ የንብ ውጤቶች ማከማቻ ክፍል፣ የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣ ማሸጊያና ሌብል ማድረጊያ ክፍል፣ የተጣራ የንብ ውጤቶች ማከማቻ ክፍል፣ አነስተኛ ላብራቶሪ፣ የዕቃዎች ማከማቻ ክፍል፣ ጽ/ቤት እና የፍሳሽ ማስወገጃ ማሟላት አለበት፤

2) የሚገነቡት ክፍሎች በቀላሉ ማፅደት እንዲቻል ወለሉና ግድግዳው መታጠብ የሚችል እንዲሁም ሙቀትና ዕርጥበት ለመቆጣጠር አየር እንዲያዘዋወርና መርዛማ ካልሆኑ ቁሳቁሶች መገንባት አለበት፤

3) የንብ ውጤቶች ሲከማቹ ከወለሉ ጋር ቀጥታ ግንኙነት እንዳይኖረው ወለሉ ላይ መደርደሪያ ሊኖር ይገባዋል፤

4) ለንብ ውጤቶች ማቀነባበር የሚውል ህንፃ የሚገነባበት ቦታ የንብ ውጤቶችን ከሚበክሉ ባዕድ ነገሮች 50 ሜትር መራቅ አለበት፤

5) ለንብ ውጤቶች ማቀነባበር የሚውል ህንፃ የሚገነባበት ቦታ ከፋብሪካ ጭስ ቢያንስ 2 ኪ.ሜትር የራቀ መሆን አለበት፤

6) ለንብ ውጤቶች ማቀነባበር የሚውል ህንፃ በሚገነባበት ቦታ መሰረታዊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች የተሟሉበት ወይም ባለቤቱ ማሟላት የሚችል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

## 13. ስለንብ ውጤቶች ማቀነባበርያ፣ ማሸጊያ ቁሳቁሶችና ስለምልክት አደራረግ

1) ማንኛቸውም ለንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ የሚውሉ ቁሳቁሶች ተቆጣጣሪው አካልና ደረጃ ለማውጣ ስልጣን የተሰጠው አካል ባወጣው ደረጃ መሰረት መስፈርቱን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡
2) ማንኛውንም የንብ ውጤት በማቀነባበርና ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ከተመሳሳይ አካባቢዎች በተመሳሳይ ወቅት የሚሰበስባቸው የንብ ውጤቶች ለይቶ ማቀነባባርና ማሸግ አለበት፡፡
3) ማንኛውንም የንብ ውጤት አቀነባብሮና አሽጎ ለገበያ የሚያቀርብ ሰው በማሸጊያ እቃው ላይ ተቆጣጣሪው አካል ባወጣው መስፈርት መሰረት ስለምርቱ የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ መለጠፍ አለበት፡፡

## 14. ስለ ንብ ውጤቶች ምርት አከመቻቸትና አጓጓዝ

1) ማንኛውም የንብ ውጤቶች የሚከማችበት ቦታ ንፅህናው በተጠበቀና ደረቅ ፣ለፀሐይ ብርሃን ያልተጋለጠና በቂ የአየር ዝውውር ባለው ቦታ መሆን አለበት፡፡
2) ማንኛውም የንብ ውጤቶች መያዣና ማከማቻ ዕቃ ንፅህናው በጠበቀ ደረቅ፣ ምንም ዓይነት ሽታ የሌለው፣ አየር በማያስገባ መልኩ የሚከደንና ለዚህ ስራ የተፈቀዱ ቁሳቁሶች መሆን አለባቸው፡፡
3) ማንኛውም ሰው የንብ ውጤቶች በሚያጓጓዝበት ወቅት የሚከተሉትን የንፅህና መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡
   ሀ) ማጓጓዣውን የንብ ውጤቶች ከመጫኑ በፊት ማጽዳትና ከሌሎች ማጓጓዣ መለየት፤
   ለ) የመጫኛ መሳሪያ ማጽዳትና ንፁህ ማድረግ፤
   ሐ) በበሽታ ወይም በሕመም ማለትም በተቅማጥ፣ በአጣዳፊ የመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽን፣ በሳልሞኔላ፣ ሺጌላ ዝርያ፣ ኢ.ኮሊ ዝርያ፣ ሂፒታይተስ ኤ ቫይረስ ምክንያት በተከሰተ በሽታ እና በምግብ ሊተላለፉ የሚችሉ ሌሎች ኢንፌክሽኖች

የተያዘ ማንኛውም ሰው የንብ ውጤቶች በሚጫኑበት ወቅት ወደ ማጓጓዣው እንዳያጓጉዝ ወይም እንዳይጭን ማድረግ፤

መ) ዕርጥበት ለመከላከል በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ የንብ ውጤቶች መያዥ ዕቃዎች መጠቀም፤

ሠ) ውሃ የማይቆጥሩ ሽራዎች ወይም ሌሎች ተስማሚ ሽፋኖች መጠቀም፤

4) ማንኛውም የንብ ውጤቶች በሚጓጓዝበት ወቅት ከሌሎች የንብ ውጤት ካልሆኑ ምርቶች ጋር መጫን አይፈቀድም፡፡

## ክፍል አምስት

## የንብ ሀብትና የንብ ቀሰም ዕጽዋት አጠባበቅ እና የአናቢ ግዴታ

### 15. የንብ ሀብት ጥበቃ

1) ማንኛውም የዕፅዋት ጥበቃና ሌሎች ስራዎችን የሚያካሄድ ሰው ፀረ-ተባይ እና ሌሎች ኬሚካሎችን መጠቀም ያለበት ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ብቻ መሆን ያለበት ሲሆን መጠቀም ግዴታ ሆኖ ከተገኘ በሚጠቀምበት ወቅት አግባባዊ ባልሆነ አጠቃቀም ምክንያት ንቦችንና የንብ ዉጤቶች እንዳይመረዙና በንቦች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የሚከተሉትን ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

ሀ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭትን በሰው ጉልበት፣ በመኪና ወይም በአይሮፕላን በሚያከናውንበት ወቅት ቢያንስ በ4 ኪሎ ሜትር ዙሪያ ንቦች መኖራቸው ከተረጋገጠ ከ72 ሰዓት በፊት ለንብ አናቢዎች ወይም ለሚመለከተው አካል መቼ፣ የት ቦታ እና በስንት ሰዓት፣ ለምን ያክል ጊዜ እና ምን አይነት ኬሚካል እንደሚረጭ ማሳወቅ አለበት፤

ለ. የኬሚካል ርጭቱ በንብ እርባታው አቅራቢያ ባሉ የሰብል ማሳዎች ላይ አረሞች ሣያብቡ ወይም ከቀኑ 11 ሰዓት በኃላ መካሄድ አለበት፤

ሐ. በሰብል ላይ የሚረጩ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የቆይታ ጊዜያቸው አጭር ሆኖ ተባዮችን ውጤታማ በሆነ መልኩ መቆጣጠር የሚችሉና ከአካባቢ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው፤

መ. በጥቅም ላይ የሚውሉት ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በተቆጣጣሪው አካል የተመዘገቡና የአጠቃቀም መመሪያ በመያዣ እቃዎቻቸው ላይ ያላቸው መሆን አለባቸው፤

ሰ. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከመጠቀሙ በፊት የአጠቃቀም መመሪያውን በደንብ ማወቅ እና መጠቀም አለበት፤

ረ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭት በሚካሄድበት ወቅት ከፍተኛ ነፋስ የሚኖር ከሆነ ኬሚካሉ በንቦች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ምንም ዓይነት ርጭት መካሄድ የለበትም

ሠ. ለኬሚካል ርጭት ጥቅም ላይ የዋሉ መርጫ መሳሪያዎች፣ አልባሳት እና የተሌያዩ ቁሳቁሶች ታጥበው እና ደርቀው በተገቢው ቦታ መቀመጥ አለባቸው፤

ሸ. የቁሳቁሶች እጣቢ ንቦች ባሉበት አቅራቢያና በውሀ ኣካላት ላይ እንዳይደፉ በማድረግ በጥንቃቄ መወገድ አለበት፤

ቀ. ባዶ የፀረ ተባይ መያዣ ዕቃዎችን ሶስት ጊዜ በውሃ በማለቅለቅ ተበሳስተው እንዲቀመጡና ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መወገድ ይኖርባቸዋል፤

በ. የፀረ-ተባይ ኬሚካል ርጭቱን የጊዜ ሠሌዳ እንደ አካባቢው የአየር ንብረት ተለዋዋጭነት በመከታተል እንዲቀያየር ማድረግ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሱትን ስራዎች ለመተግበር በሰብል፣ በእንስሳት፣ በአካባቢ ጥበቃ እና በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ተሰማርተው የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መስራት አለባቸው፡፡

3) የተቀነባበሩ የንብ መኖዎች በሀገር ውስጥ ለማምረት ወይም ከውጭ ሀገር ለማስገባት የሚፈልግ ሰው ከሚመለከተው አካል የብቃት ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጪ የሚገቡና በሃገር ውስጥ የሚመረቱ የተቀነባበሩ የንብ መኖዎች ተቆጣጣሪው አካል የሚያወጣውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

## 16. የንብ ቀሰም ዕፅዋት ጥበቃ

1) ማንኛውም ሰው ለምርምር ወይም ለሌላ ተግባር የማር ዕፅዋት ዝርያዎችን ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ሲፈልግ ከተቆጣጣሪው አካል የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡

2) የማር ዕፅዋት ዝርያው ለተጠቃሚዎች ከመሰራጨቱ በፊት በተለያዩ ስነ ምህዳሮች ሙከራ ከተደረገ በኋላ ውጤታማነቱ በተቆጣጣሪ አካል መረጋገጥ አለበት፡፡

## 17. የአናቢ ግዴታዎች

1) ማንኛውም አናቢ የንብ እርባታ ሲያካሂድ በንቦች ላይ ጉዳትና እልቂት እንዳይደርስ የሚከተሉት ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡፡

   ሀ. አናቢው የተሟላ የንብ መከላከያ ትጥቅ ማለትም ቱታ፣ ቦት ጫማ፣ ጓንት እና አይነርግብ እና ሌሎች መከላከያዎችን መጠቀም፤

   ለ. ንቦችን የሚያስቆጣ ሽቶ፣ ከፍተኛ ጭስ፣ፊካ ያላሉና ንፅህናቸው ያልተጠበቁ አልባሳት፣ ማሩን የሚበክል የኩበት ጭስ፣ ኬሚካል እና ሌሎች ነገሮችን አለመጠቀም፤

   ሐ. አናቢው የግልና የጋጣውን ስፍራ ንፅህና መጠበቅ ፤

2) ማንኛውም አናቢ የኬሚካል ርጭት በአካባቢው እንደሚደረግ በተገለፀለት ጊዜ ምን አይነት ኬሚካል እንደሚረጭ ከባለሞያ ካረጋገጠ በኃላ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡፡

   ሀ. የኬሚካሉ ባህሪ ከተረጨ በኃላ ቅሬቱ ለረጅም ሰዓታት (ከ 24 ሰዓት በላይ) በተክሉ እና አካባቢው ላይ የሚቆይ መሆኑ ከታወቀ ህብረ-ንቡን ከሚረጭበት ቦታ ቢያንስ 5 ኪሎሜትር ርቀት ቦታ በመውሰድ እንደ ሁኔታው ለ1 ሳምንት ማቆየት አለበት፤

   ለ. ኬሚካሉ ከተረጨ በኃላ ቅሬቱ ከ24 ሰዓት በታች ጊዜ የሚቆይ መሆኑ ከታወቀ ህብረ-ንቡን ለ1 ቀን ከቀፎው እንዳይወጡ አድርጎ በመመገብ ማቆየት አለበት፤

3) የማነብ ስራ የሚያካሄድ ማንኛውም አናቢ ሕብረ-ንቦቹ በሰው እና በቤት እንስሳት ላይ አደጋ እንዳያደርሱ የሚከተሉትን ቅድመ ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡-

   ሀ. በአካባቢው የንቦች ቁጣን ሊያስከትል የሚችል ሽታ ማለትም ሽቶ፣ ትኩስና የከረመ የአዛባ ሽታ፣ አዲስ የተቆፈረ የመሬት ሽታ እና ሌሎች ሽታዎች እና ከፍተኛ ድምፅ እንዳይኖር ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤

   ለ. በአካባቢው ንብ የማነብ ስራ ስለመኖሩ የሚገልፅ በቢጫ መደብ ላይ በጥቁር ቀለም የሰራተኛ ንብ ምስል ያለበት በግልፅ የሚታይ ልዩ ምልክት እንዲኖር ማድረግ አለበት፡፡

4) ህብረ-ንቦችን በማዟዟር የሚያናባ አናቢ ንቦችን ማዟዟር የሚችለው የንብ ንዑስ ዝርያዎች በሚገኙበት ስነ-ምህዳር ውስጥ ብቻ መሆን አለበት፡፡

5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አናቢ ህብረ-ንቦቹን ከማዟዟሩ በፊት ህብረ-ንቡ ከበሽታ ማለትም አሜባ፣ ኖሴማ እና ከተባዮች ማለትም

የሰምበል ትል፣ የንብ መኸገር እና ከንብ ቅማል በተለይ ከቫሮዋ ቅማል ነጻ መሆናቸው በባለሙያ መረጋገጥ አለበት፡፡

6) በዑደት ወቅት ከሌላ ቦታ የተያዘ ወይም በግዥ የተገኘ አዲስ ህብረ-ንብ ከበሽታ ነፃ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ እንዲቻል ለ14 ቀናት ከነባር ህብረ ንቦች ጋር መቀላቀል የለባቸውም፡፡

## ክፍል ስድስት

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና የመዝገብ አያያዝ

### 18. የብቃት ማረጋገጫ ስለመስጠት

1) ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 እና 20 ስር የተጠቀሱትን መስፈርቶች በማሟላትና በዕዝል 01 ስር የተመለከተውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለተቆጣጣሪው አካል ማቅረብ አለበት፡፡
2) የድርጅቱ ዝግጅትና ማመልከቻ የተሟላ ሲሆን ከተቆጣጣሪው አካል የተውጣጡ ሶስት አባላት ያሉት ባለሙያዎች በመላክ እንዲታይለት ይደረጋል፡፡
3) አስፈላጊውን መስፈርት ስለመሟላቱ የተቆጣጣሪው አካል ባለሙያዎች በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሟላታቸውን በመፈተሸና በማረጋገጥ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
4) ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ በተቆጣጣሪው አካል ከተረጋገጠ በኋላ የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻውን ካስገባበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 የስራ ቀናት ውስጥ ይሰጠዋል፡፡
5) ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት ካላሟላ መስፈርቶቹን እንዲያሟላ በጽሑፍ ይገለፅለታል፡፡
6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ 5 መስፈርቶችን እንዲያሟላ በጽሑፍ የተገለፀለት ድርጅት መስፈርቶቹን ማሟላቱን በባለሙያዎች ሪፖርት ቀርቦ ከተረጋገጠ በኋላ ከ10-15 ባሉት የስራ ቀናት የብቃት ማረጋገጫው ይሰጠዋል፡፡
7) በዚህ አንቀጽ መሰረት የብቃት ማረገገጫ የተሰጠው ሰው በመስፈርቱ መሰረት እየሰራ ስለመሆኑ በየዓመቱ በተቆጣጣሪው አካል ኦዲት ይደረጋል፡፡

## 19. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መሰረታዊ መስፈርቶች

1) ማንኛውም ሰው ለንግድ በንብ ልማት ብቃት ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

ሀ. ከልማቱ ስለሚመረተው የንብ ውጤቶች የንግድ አዋጭነት ዕቅድ ማዘጋጀትና ማቅረብ፤

ለ. የማልሚያ ቦታው የይዞታ ማረጋገጫ ወይም የኪራይ  ውል ስምምነት ማቅረብ፤

ሐ. በልማቱ መስክ አግባብነት ያለው የትምህርት ዝግጅት እና ክህሎት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ወይም አግባብነት ያለው ባለሙያ መቅጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፤

መ. የንግድ አዋጭነት ዕቅድ መሠረተ ልማቱን ለማካሄድ በቂ ካፒታል ያለው ስለመሆኑ የባንክ ማስረጃ ማቅረብ፤

ሠ. እንዲያገግሙ በተከለሉ ቦታዎች፤ በማህበራት ደን፤ ፖርኮችና ጥብቅ ቦታዎች ላይ የሚያንብ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የጽሑፍ ስራ ፈቃድ ማቅረብ፤

2) ማንኛውም ሰው ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል ለማቋቋም የብቃት ማረጋገጥ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

ሀ. ንግስት ንብን በማባዘት ስለሚገኘው ውጤት የንግድ አዋጭነት ዕቅድ ማዘጋጀትና ማቅረብ፤

ለ. የማልሚያ ቦታው የይዞታ ማረገገጫ ወይም የኪራይ  ውል ስምምነት ማቅረብ፣

ሐ. በልማቱ መስክ አግባብነት ያለው የትምህርት ዝግጅት እና ክህሎት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ወይም አግባብነት ያለው ባለሙያ መቅጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፤

መ. የንግድ አዋጭነት ዕቅድ መሠረት ልማቱን ለማካሄድ በቂ ካፒታል ስለመኖሩ የባንክ ማስረጃ ማቅረብ፤

ሠ. እንዲያገግሙ በተከለሉ ቦታዎች፤ በማህበራት ደን፤ ፓርኮችና ጥብቅ ቦታዎች ላይ የሚያንብ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ ማቅረብ፤

3) ማንኛውም ሰው የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት ለማቋቋም የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

ሀ. የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረት ሥራ በመለየት የንግድ አዋጭነት ዕቅድ አዘጋጅቶ ማቅረብ፤

ለ. የመሸጫ ቦታ እና መጋዘን የይዞታ ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል ስምምነት ማቅረብ፣

ሐ. የመሸጫ ቦታ እና መጋዘኑ ከተለያዩ ኬሚካሎች፣ ኬሚካላዊ ይዘትና የመትነን ባህሪይ ያላቸው ምርቶች ከሚመረቱበት ፋብሪካዎች አካባቢ ቢያንስ 50 ሜትር የራቀ መሆን አለበት፤

መ. በንግድ አዋጭነት ዕቅዱ መሠረት ለሥራው ማከናወኛ በቂ ካፒታል ስለመኖሩ የባንክ ማስረጃ ማቅረብ፤

4) ማንኛውም ሰው የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ለማቋቋም የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤

ሀ. ለማቀነባበርና ለማሸግ የተፈለገውን የንብ ውጤት/ቶች በመለየት የንግድ አዋጭነት ዕቅድ ማዘጋጀት፣

ለ. ለማቀነባበርና ለማሸግ ሥራ የሚያስፈልግ ግንባታ ለማካሄድ ኬሚካላዊ ይዘትና የመትነን ባህሪይ ያላቸው ምርቶች ከሚመረቱበት ፋብሪካዎች አካባቢ ቢያንስ 50 ሜትር የራቀና አቧራና ብናኝ የሌለበት ቦታ ማዘጋጀት፣

ሐ. የግንባታ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ውል ስምምነት ማቅረብ፣

መ. በንግድ አዋጭነት ዕቅዱ መሠረት ለሥራው ማከናወኛ በቂ ካፒታል ስለመኖሩ የባንክ ማስረጃ ማቅረብ፤

ሠ. በመስኩ አግባብነት ያለው የትምህርት ዝግጅት እና ክህሎት ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ወይም አግባብነት ያለው ባለሙያ መቅጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፤

ረ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

## 20. የግዴታ ወረቀት የሚፈረምባቸው ሁኔታዎች

1) **ማንኛውም በንግድ ንብ ልማት እና በንግድ ንግስት ንብ ርቢ መሰማራት የሚፈልግ ሰው፡-**

ሀ. ሕይወት ያላቸው ንቦች፣ ያገለገሉ ቀፎዎች፣ የንብ መገልገያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ከውጪ ገዝቶ ላለማስገባት፤

ለ. ማንኛውንም ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ የንብ ውጤቶች በጥራትና ደህንነት እንዲመረቱ የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ጠብቆ ለመስራት፤

ሐ. የተቆጣጣሪው ባለስልጣን ኢንስፔክተር ማንኛውንም ዓይነት ኢንስፔክሽን ለማካሄድ በሚቀርብበት ጊዜ ፈቃደኛ የመሆን ፤

መ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶች አደራጅቶ መያዝ፣ የምርቱን የሥርጭት አውታር መረጃ መያዝና ለምርመራና ክትትል አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከታቸው አካላት ግልጽ የማድረግ፣

ግዴታ አለበት፡፡

2) **ማንኛውም የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት ማቋቋም የሚፈልግ ሰው፡-**

ሀ.ጥራትና ደረጃውን በጠበቀ የንብ ቀፎ ጥሬ ዕቃ፣ መሣሪያና ቁሳቁስ የማምረት፣

ለ.ተቆጣጣሪው አካል ስለማሽኖች፣መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች እና የምርት ጥራትና ክምችት ፍተሻ ለማድረግ በሚጠይቅበት ጊዜ የመተባበር፣

ሐ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶች አደራጅቶ መያዝ፣ የምርቱን የሥርጭት አውታር መረጃ መያዝና ለምርመራና ክትትል አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለተቆጣጣሪው አካል ግልጽ የማድረግ፣

ግዴታ አለበት ፡፡

3) **ማንኛውም የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ማቋቋም የሚፈልግ ሰው፡-**

ሀ. የንብ ውጤቶችን ምንጭ፣ ዓይነትና ጥራት ለይቶ ማቀነባበርና ማሸግ እንዲሁም የጥራት ደረጃና ደኅንነት ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጪ ገበያ የማይመጥን ሆኖ ሲገኝ ከምንጩ ችግሩን መለየት፣ ማሻሻልና ዳግም እንዳይከሰት የመከታተልና የማረም ግዴታ፤

ለ. ማንኛውንም ስለንብ ውጤቶች ጥራትና ደኅንነት የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ጠብቆ የመሥራት፤

ሐ. ተቆጣጣሪው አካል የቁጥጥርና የፍተሻ ስራ እንዲያካሂድና የንብ ውጤቱን የሚያሰባስብበትን አካባቢ የማስፈተሽ፣

ግዴታ አለበት፡፡

## 21. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለመስጠት

ማንኛውም ሰው ቀደም ሲል የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲበላሽበት ወይም ሲጠፋበት ወይም ሲወድምበት ምትክ ሊያገኝ የሚችለው፡-

1) ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ከሆነ ከነብልሽቱ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስና ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ፤
2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ከሆነ ወይም ከወደመበት ስለመጥፋቱ ወይም ስለመውደሙ የሚገልጽ ማረጋገጫ ከሚመለከተው አካል ሲያቀርብና ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ፤

## 22. የመዝገብ አያያዝ

ማንኛውም በንግድ ንብ ልማት፣ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣ የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት፡-

1) ለሚያመርታቸው የንብ ውጤቶች፣ ለሚያባዛቸው ንቦች፣ ለሚያስመጣቸውና ለሚያከፋፍላቸው ጥሬ እቃዎች ወይም ግብአቶች ምንጭና ስለሚሸጣቸው የንብ ውጤቶች መነሻ ዝርዝር መረጃ ለይቶ የመያዝ፡፤
2) ስለአመረተው ወይም ስላስመጣው፣ ስለአከፋፈለው፣ ስለላከው፣ ስለተበላሸው፣ የመጠቀሚያ ጊዜ ስላለፈበት ሌሎችም ከንብ አያያዝ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች በአግባቡ የመያዝና በተቆጣጣሪው አካል ወይም አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ የማሳየት፤
3) የንብ ውጤቶችን ወይም ግብአቶችን የገዛበትና የሸጠላቸውን ድርጅቶች ስምና ሙሉ አድራሻ በዝርዝር መያዝ፤
4) ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ወቅታዊ የማድረግ፣በአግባቡ የመያዝና ለተቆጣጣሪው አካል ወይም አግባብ ላለው አካል ግልጽ ማድረግ፤

አለበት፡፡

# ክፍል ሰባት

# አስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድ

## 23. ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሚያሳግድ፣ ከሚያሰርዝ ወይም ሌሎች ከባድ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ከሚያስወስድ ጥፋት ውጪ ያሉ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎችን መተላለፍ በተቆጣጣሪው አካል እንደአግባቡ የቃል ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥባቸው ይችላል፡፡
2) አናቢው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 5 የተጠቀሱትን ግዴታዎች ተግባራዊ ሳያደርግ ቢገኝና የሚያሂዙራቸው ህብረ ንቦች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በተለይ ተላላፊ በሆኑ በሽታዎችና ተባዮች የተጠቁ መሆናቸው የተረጋገጠ ከሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት፡-
   ሀ. ህብረ-ንቦቹን ወደ ቀድሞው ቦታ በመመለስ አስፈላጊው ህክምናና እንክብካቤ በአናቢው ወጪ እንዲሸፈን ይደረጋል፤
   ለ. ህብረ-ንቦቹ በበሽታ ወይም በተባይ የተጠቁበት ደረጃ በባለሙያ ከታየ በኋላ የማይሻላቸው ወይም የማያገግሙ ከሆነ በአናቢው እንዲወገዱ ይደረጋል፤ ሆኖም ግን አናቢው ማስወገድ ካልቻለ በተቆጣጣሪው አካል እንዲወገድ ተደርጎ ወጪው አናቢው እንዲሸፍን ይደረጋል፤
   ሐ. በተቆጣጣሪ አካል ማረጋገጫ ሳያገኝ አናቢው በሚያሂዙራቸውና በሌሎች ህብረ-ንቦች ወይም በሰዎችም ሆነ በእንስሳት ላይ የበሽታ፣ የተባዮችና ሌላ ማናቸውም ዓይነት ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ከተገኘ ወይም ካስከተለ በወንጀል ህጉ ተጠያቂነት እንዳለበት ሆኖ አግባብ ባለው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 24. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እገዳ

ማንኛውም በንግድ ንብ ልማት፣ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣ የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በተቆጣጣሪው አካል ጉድለቶቹ

እስኪስተካከሉ ድረስ ለዘመኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን እስከ ሶስት ወራት ለሚደርስ ጊዜያት ሊያግድ ይችላል፡፡

1) ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን ከሶስት ወር በፊት ሳያሳውቅ የድርጅቱን የቦታና የአድራሻ ለውጥ ካደረገ፤
2) ተቆጣጣሪው ባለስልጣን በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው የቁጥጥር ስራዎች እንዳያከናውን ለመተባበር ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ካሰናከለ፤
3) ከሁለት ጊዜ በላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ድርጅቱን የማያስተካክል ከሆነ ወይም መመሪያው ባስቀመጠው መሰረት ተግባሩን ካልፈጸመ፤

## 25. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

ማንኛውም በንግድ ንብ ልማት፣ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣ የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ተቆጣጣሪው አካል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊሰርዝበት ይችላል፡-

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ መመሪያው ከሚፈቅደው አሰራር ውጭ በሆነ መንገድ የተገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
2) በማናቸውም መንገድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ለሌላ ወገን አስተላልፎ ከተገኘ፤
3) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ከወጣበት ዓላማ ውጭ ሲሰራ ከተገኘ፤
4) ስለምርቱ ሁኔታ ገላጭ ጽሁፍ የሌለው፣ የንብ ውጤቶችን የከለሰ፣ አስመስሎ ያቀረበ፣ ደረጃቸውን ያልጠበቁ የማናቢያ ቁሳቁሶችና የንብ ውጤቶች ለገበያ ያቀረበ ወይም በማናቸውም ሁኔታ በህገወጥ ንግድ ውስጥ ገብቶ የተገኘ፤
5) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በወቅቱ ያላሳደሰ እንደሆነ፤
6) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 24 መሰረት እገዳ ተጥሎበት ጉድለቶቹን ያላስተካከለ እንደሆነ፣

## 26. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን ስለመመለስ

1) ማንኛውም ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣ የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣ የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ

ምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት አይነትና የቦታ ለውጥ ሲያደርግና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጠይቆ ተቀባይነት ሲያገኝ ነባሩን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለተቆጣጣሪው አካል ወዲያዉኑ መመለስ አለበት፡፡

2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘ፣ በተቀመጠው የእድሳት ጊዜ ገደብ ሳይታደስ ከቀረ ወይም በራሱ ፈቃድ የንግድ ስራውን ካቋረጠ ድርጅቱ ነባሩን ፈቃድ በአንድ ወር ጊዜ የስራ ቀናት ውስጥ ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን መመለስ አለበት፡፡

## 27. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እገዳ ስለማንሳትና የተሰረዘውን ስለመተካት

1) ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የታገደበት በንግድ ንብ ልማት፣ለንግድ ንግስት ንብ ርቢ ጣቢያ ወይም ማዕከል፣የማናቢያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ ማምረቻ ድርጅት፣የንብ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ድርጅት የተጣለበት እገዳ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ጥፋቱን አምኖ ሲያስተካክል በባለስልጣኑ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ማንኛውም ድርጀት በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝና ለስረዛ ያበቃውን ጥፋት ሙሉ ለሙሉ በማረምና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ የተደረገው ማስተካከያ በባለስልጣኑ በባለሙያዎች ተረጋግጦ በተሰረዘው የምስክር ወረቀት ምትክ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

# ክፍል ስምንት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 28. ግንዛቤ ስለመፍጠር

ይህ መመሪያ የሚያስፈጽሙ አካላት በዚህ መመሪያ ላይ ስለተመለከቱ ጉዳዩች የምክርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስጠት አለባቸው፡፡

## 29. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 30. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በግብርና ሚኒስቴር ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበና በተቋሙ ድህረ ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

መስከረም/2017 ዓ/ም

አዲስ አበባ

ዶ/ር ግርማ አመንቴ

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር

# ዕዝሎች

## ዕዝል 01

**የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ማመልከቻ ቅጽ 01**

**ቁጥር፡ ------------------------------**

**ቀን፡--------------------------------**

**ለኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን**

**ለ ----------------------------------------- ዴስክ/መሪ ስራ አስፈፃሚ**

<u>አዲስአበባ</u>

ጉዳዩ፡ **የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ስለማቅረብ**

የአመልካች ግለሰብ/ተቋም/ ድርጅት ስም ---------------------------------------------------------

የንግድ ስም -------------------------------------------------------------------------------------

የንግድ/ድርጅት/ተቋም አድራሻ፡

ክልል ---------------------------- ክ/ከተማ ------------------------------ ወረዳ-------------------

የቤት ቁጥር ----------------የድርጅት ምዝገባ ቁጥር---------------- የንግድ ፈቃድ ቁጥር-------

የስልክ ቁጥር፡ ሞባይል ------------------------ የቢሮ ------------------------

በአዋጅ ቁጥር 980/2008 በተደነገጉት ሁኔታዎች ላይ በመመሥረት የግብርና ሚ/ር በዘርፉ ለሚሰማሩ አካላት ባዘጋጃቸው የንግድ ሥራ መደቦች ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት መመሪያ መሠረት የ------------------------------------------------------------------------------------------------

ሥራ ለማካሄድ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

በግልጽ የሚነበብ የድርጅቱ ማህተም ፊርማ

ሥራ አስኪያጅ (ተወካይ)

## ዕዝል 02

**የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጽ 02**

ቁጥር፡ -------------------------

ቀን፡ ------------------------

**ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር**

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡ **የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት**

------------------------------------------------------------------ የተባለግ/ል/ኃ/የተ/የግ/ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 980/2008 በተደነገገውና ሚኒስቴር መ/ቤታችን በ----------------- ዓ.ም ባወጣው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት መሠረት፣ለ---------------------------------------------- ----------- ሥራ የፈቃድ መስጫ መደብ ቁጥር --------------------------- ላይ የተቀመጡትን መመዘኛዎች፡

1 ----------------------------------------------------------------------------------------------------

2 ----------------------------------------------------------------------------------------------------

3 ----------------------------------------------------------------------------------------------------

4 ----------------------------------------------------------------------------------------------------

5 ---------------------------------------------------------------------------------------------------------

አሟልቶ የተገኘ ተቋም ስለሆነ ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

ከሰላምታ ጋር